አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

3

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአቂዳ ትምህርት

በቴሌግራም

2

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# ሁለተኛው አለም አቀፍ የርቀት ትምህርት መሪ ቃል
# “ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው”




**“አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው ፡፡”**

ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ
የአፍሪካ አካዳሚ
የርቀት ትምህርት
1441 ሒጅሪያ/2020

ሶስተኛው ተውሂዱል አስማእ ወሲፋት (አላህን በስሞቹና በባህሪያቱ አንድ ማደረግ)

## አላህ (ሱ.ወ) ከኛ ጋር ነውን?

አዎ! አላህ (ሱ.ወ) ከኛ ጋር ነው፡፡
ሆኖም ከኛ ጋር ነው ሲባል በዛቱ (በአካሉ) ማለት ሳይሆን፤ በእውቀቱ፤ በመስማቱ፤ በማየቱ፤ በመጠበቁ፤ እውቀቱ በማካበቡ፤ በችሎታውና በፍላጎቱ ከኛ ጋር ነው ማለት ነው፡፡ ዛቱ ግን የፍጡሮችን ዛት ፈፅሞ አይደባለቅም፡፡ የትኛውም ፍጡር ቢሆን በሱ ላይ እውቀቱ አያካብብም፡፡ ስለዚህ በዛቱ ከእኛ ጋር ነው አይባልም፡፡

## የአላህ ስሞች ምን ምን ናቸው?

አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን (ለአላህ መልካም ስሞች አሉት፡፡ እናም (ስትጸልዩ) በነርሱ ጥሩት አለ፡፡

ነቢዩም ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ለአላህ ዘጠና ዘጠኝ ለመቶ አንድ የጎደለው ስሞች አሉት፡፡

እነሱን በቃሉ የሐፈዛቸውና የተገበራቸው ጀነት ይገባል›› ብለዋል፡፡

እነሱን በቃሉ የሐፈዛቸው የሚለው፡-

አንደኛ፡- ቃላቸውንና ቁጥራቸውን መሀፈዝ፤

ሁለተኛ፡- ትርጉማቸውንና መልዕክታቸውን ማወቅ በሱም ማመን ነው፡፡

ለምሳሌ (አል-ሐኪሙ) ጥበበኛው ስንል ሁለንተናዊ ጉዳዮቻችንን ለአላህ መስጠት አለብን ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ነገር የሚሆነው በጥበቡ ብቻ ነውና፡፡

(አል-ቁዱስ) ንፁህ ስንል አላህ ከሁሉም ነውርና ጉድለት የፀዳ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በቀልባችን እናስታውሳለን፡፡

## የአላህን ስሞችና ባህሪያት ማወቁ ጥቅሙ ምንድን ነው?

አላህ የሰው ልጅ በአንደኛ ደረጃ እንዲያውቀው ግዴታ ያደረገው ነገር እሱን ማወቅን ነው፡፡
ምክኒያቱም ሰዎች ካወቁት በትክክል ይታዘዙታል፡፡
አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ላይ እንዲህ አለ (ከአላህ በስተቀር የእውነት አምላክ አለመኖሩን እውቅ ለወንጀልህም ምህረትን ለምን) አለ፡፡
አላህን (ሱ.ወ) በርህሩህነቱ ማውሳቱም ከሱ ቅጣትና ቁጣ ፍርሃት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡
ፀጋን በመቸር ብቸኛ መሆኑን ማውሳትም እንድናመሰግነው ያደርገናል፡፡ በአጠቃላይ በአላህ መስራት ነው፡፡ ከአላህ (ሱ.ወ) ስሞችና ባህሪያት መካከል የሰው ልጅ የሚገለፅበትና የሚወደስበት አለ፡፡ በእነሱ ከተገለፀበትና የሚመሰገንበት ብሎም የሚታዘዝበት አላህ (ሱ.ወ) ግን የማይገለፅበት ባህሪ አለ፡፡ እሱም አገልጋይነት፤ ድህነት፤ ከጃይነት፤ የበታችነት፤ ልመናና የመሳሰሉትን ነው፡፡
አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ በጣም የተወደደ ማለት አላህ (ሱ.ወ) የሚወደውን ባህሪ የተላበሰ ሰው ነው፡፡
የተጠላ ማለት ደግሞ እሱ በሚጠላቸው ባህሪያት የተገለፀ ነው፡፡

## አላህ (ሱ.ወ) ከኛ ጋር ነውን?

አዎ! አላህ (ሱ.ወ) ከኛ ጋር ነው፡፡

ሆኖም ከኛ ጋር ነው ሲባል በዛቱ (በአካሉ) ማለት ሳይሆን፤ በእውቀቱ፤ በመስማቱ፤ በማየቱ፤ በመጠበቁ፤ እውቀቱ በማካበቡ፤ በችሎታውና በፍላጎቱ ከኛ ጋር ነው ማለት ነው፡፡ ዛቱ ግን የፍጡሮችን ዛት ፈፅሞ አይደባለቅም፡፡

የትኛውም ፍጡር ቢሆን በሱ ላይ እውቀቱ አያካብብም፡፡ ስለዚህ በዛቱ ከእኛ ጋር ነው አይባልም፡፡

## አላህ (ሱ.ወ) በአይን ይታያልን?

ወደ ቂብላ የሚሰግዱ ሙስሊሞች ሁሉ አላህ በዚህ ዓለም እንደማይታይና አማኞች በመህሸር ቀንና በጀነት እንደሚያዩት ተሰማምተዋል፡፡
አላህ በቁርአኑ:-
(ፊቶች በዚያ ቀን አብሪዎች ወደ ጌታቸው ተመልካቾች ናቸው) ብሏል፡፡

## በአላህ (ሱ.ወ) ስሞችና በባህሪያቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የአላህ ሱ.ወ ስሞችና ባህሪያቱ በነሱ በኢስቲዓዛ /በአላህ በመጠበቅ/ እና በእነሱም በመማል በመፈቀዱ ላይ ሁለቱም የጋራ ተልዕኮ ሲኖራቸው እንዲሁ በመሐከላቸው ብዙ ልዩነቶችም አሉ፡፡

ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**1ኛው፡-** በባህሪያቱ ሳይሆን በስሙ አላህን ማምለክና መለመን የሚቻል ሲሆን በስሙ አላህን ማምለክ ሲባል ለምሳሌ አብዱልከሪም የቸሩ ጌታ ባሪያ ዐብዱሏህ/ የአላህ ባሪያ፤ ዐብዱረህማን /የረህማን ባሪያ/፤ ብሎ መሰየም ይቻላል፡፡ በባህሪያቱ ግን ለምሳሌ ከረም /ልግስና/ በሚለው ባህሪው /ዐብዱልከረም/ የልግስና ባሪያ/ ተብሎ መሰየም ግን አይቻልም፡፡ በዱዓም ያከሪም ብሎ አላህን መለመን የሚቻል ሲሆን ያከረመ አሏህ (ሱ.ወ) ብሎ መለመን ግን አይቻልም፡፡

**2ኛው፡-** ከአላህ (ሱ.ወ) ስሞች ባህሪ ይወሰዳል፡ ለምሳሌ አር-ረህማን/አዛኝ ከሚለው ስሙ ረህመህ /እዝነት የሚለውን ባህሪ እንወስዳለን፡፡ ባህሪያቱ ግን ከነቢዩ የተሰሙ ካልሆኑ በስተቀር ቋንቋን መሰረት አድርጎ ስሞች አይመሰረቱም፡፡ ለምሳሌ ኢስቲዋእ/መደላደል/ከሚለው ስርወ ቃል ወስደን ከአላህ (ሱ.ወ) ስሞች አንዱ ሙስተዊ/ተደላዳዩ/ ነው ማለት አይቻልም፡፡

**3ኛው፡-** የአላህ ስራዎች ከነቢዩ የተሰሙ ካልሆኑ በስተቀር ቋንቋን መሰረት አድርጎ ስሞች አይመሰረቱም፡፤ ለምሳሌ ከአላህ ተግባሮች መካከል ቁጣ አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ቁጣ ከሚለው ስርዎ ቃል ወስደን ከአላህ (ሱ.ወ) ስሞች አንዱ ተቆጭ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ባህሪያቱ ግን ከተግባሮቹ ቀጥታ ይወስዳሉ፡፡ ለምሳሌ ቁጣ የሚለውን ባህሪ ለአላህ አለው እንላለን፡፡ ምክኒያቱም ቁጣ ከተግባሮቹ መካከል አንዱ ነውና፡፡